መልእክት አሥር

## የምለሳ መጻሕፍት የሆኑት የዕዝራ እና የነህምያ ማዕከላዊ እና ወሳኝ ነጥብ—
## በጌታ ምለሳ ተገቢው እና ብቁው አመራር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ነህ. 8፡1-10፤ 13፡14፣ 29-31፤
ማቴ. 20፡25-28፣ 23፡8-13፤ ዕብ. 13፡7

**I. በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚና በጌታ ምለሳ፣ አመራር በመንፈሳዊ አቅም ላይ ይመረኮዛል፤ አመራር ሹመት፣ ቋሚ፣ ድርጅታዊ ወይም የሥልጣን ተዋረድ ያለው አይደለም—1 ተሰ. 1፡5፤ 2፡1-14፤ 5፡12-13፤ ዕብ. 13፡7፣ 17፣ 24፦**

ሀ. ጌታ ስለ አመራር ያለው ፅንሰ-ሃሳብ የተፈጥሮአዊው ፅንሰ-ሃሳብ ተቃራኒ ነው፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በእርግጥም ተፈጥሮአዊ በሆነው መንገድ አመራር የለም—ማቴ. 20፡25-28፤ 23፡8-13፦

1. በእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ፣ መሪነት ማለት ባርነት ነው፤ መሪ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ባሪያ ለመሆን መፍቀድ አለበት—ማር. 10፡35-45።
2. መሪነት የሚቀረጸው በሕይወት እድገት ሲሆን የሚመጣውም አስፈላጊነት ሲኖር ነው፤ አስፈላጊነት ከሌለ፣ ምንም ዓይነት መሪነት ሊገለጥ አይችልም—1 ጴጥ. 5፡1-3።
3. የአመራርን ሰዋዊ ፅንሰ-ሃሳብ ለማስወገድ፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ያለው አመራር ሁልጊዜ በመንፈሳዊ አቅም ላይ እንዲመረኮዝ ወስኗል—ሐዋ. 13፡2፣ 9፤ 14፡12፤ ገላ. 2፡11-14።
4. በጌታ ምለሳ የተደራጀ አመራር የለም፣ አንድ የሚያደርግ ድርጅትም የለም፤ ይልቁንም፣ ለብልቶች በሙሉ በቀጥታ ትእዛዝ የሚሰጥ አንድ ራስ አለ፣ አንድ ሕይወታዊ አካል፣ አካሉ አለ—ኤፌ. 1፡22-23።

ለ. በአዲስ ኪዳን መሠረት፣ የሐዋርያት ሥልጣን መንፈሳዊ እና በቃሉ አገልግሎታቸው ውስጥ ነው—ሐዋ. 2፡42፤ 2 ቆሮ 13፡5-6፤ 1 ተሰ. 2፡13፦

1. በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ ለመግባት የሥልጣን ስፍራ የላቸውም፤ በእነርሱ የሚገለገለው ቃል ብቻ ሥልጣን አለው—ቆላ. 4፡16፤ ዕብ. 13፡7።
2. አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያትን የሚከተሉት ሐዋርያት የአዲስ ኪዳን ትምህርት ስላላቸው ነው—ፊልጵ. 2፡12 ሐዋ. 20፡17-36።
3. ቤተ ክርስቲያን ብትስት ወይም ባልሆነ አቅጣጫ ብትመራ፣ ሥልጣን ባለው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሁኔታውን ለማስተካከል ሐዋርያት ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው—ቁ. 26-27፤ 2 ቆሮ. 10፡6፤ 2 ጢሞ. 1፡13፤ 4፡2።
4. መሪነት የሚመጣው፣ የሚጠነከረው እና የሚገደበው በሐዋርያት ትምህርት ነው—ቲቶ 1፡9።

ሐ. በአዲስ ኪዳን አንድ አገልግሎት ከአንድ አመራር ጋር አለ—ሐዋ. 1፡17፣ 25፤ 2 ቆሮ. 4፡1፦

1. የዛሬው ክርስትና የተከፋፈለው ብዙ አመራሮች ስላሉ ነው፤ አገልግሎቱ አንድ ስለሆነ፣ ከአንድ አመራር በላይ መኖር የለበትም።
2. እግዚአብሔር፣ ጌታ እና መንፈስ አንድ ስለሆኑ፣ አንድ አመራር አለ፤ አንዱ አመራር ለክርስቶስ አካል የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ነው—ኤፌ. 4፡3-6።
3. አዲስ ኪዳን በመሪዎች በአገልግሎቱ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ወኪል ሥልጣን፣ ለግንባታ የሆነውን ሥልጣን ያሳየናል—2 ቆሮ. 13፡10፦
   ሀ. የእግዚአብሔር ወኪል ሥልጣን በመሪዎቹ ትምህርት ውስጥ ነበረ—1 ቆሮ. 4፡17-21፤ 7፡17፤ 11፡2፤ 16፡1፤ 2 ተሰ. 3፡6፣ 9፣ 12፣ 14።
   ለ. በሁሉም ቦታ በሁሉም ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት ነገርን ማስተማር የጳውሎስ የውክልና ሥልጣን ማሳያ ነበር—1 ቆሮ. 4፡17።

መ. በአዲስ ኪዳን አገልግሎት ውስጥ ያለው አመራር ከራሳቸው ከአዲስ ኪዳን አገልግሎት መሪዎች ይልቅ በአዲስ ኪዳን ትምህርት ውስጥ ያለ ነው—ሐዋ. 2፡42፤ 2 ጢሞ. 3፡10፦

**II. በአዲስ ኪዳን አገልግሎት ውስጥ ያለው አመራር የሚቆጣጠረው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ራእይ አመራር እንጂ የሚቆጣጠር ሰው አመራር አይደለም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ "ከሰማይ የታየኝን ራእይ እምቢ አላልሁም" ሲል አውጇል—ሐዋ. 26፡19፦**

ሀ. *የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ* በሐዋርያት በኩል ተገልጧል፣ አማኞች ግን ስለዚያ ተገቢውን መረዳት ስላጡ፣ በጌታ መመለስ ያስፈልገዋል፤ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ (በግሪኩ አይኮኖሚያ) ራሱን ለመግለጥ ቤት፣ ቤቱም ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ አካል ይኖረው ዘንድ ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን በክርስቶስ የሚያድልበት የቤተሰቡ አስተዳደር ነው—ኤፌ. 3፡2፣ 8-9፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 3፡15፤ ኤፌ. 1፡10፤ 2፡21-22፤ 1 ጴጥ. 4፡10።

ለ. *ምለሳ* ማለት አንድ ጉዳት ወይም ጥፋት ከተከሰተ በኋላ ወደ ጤናማው ሁኔታ መመለስ ማለት ነው፤ *ምለሳ* ማለት በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ይዘቶች በምለሳው አሁናዊ ግስጋሴ መሠረት በመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተገለጠው ወደ እግዚአብሔር የመጀመሪያ ውጥን እና መሥፈርት መመለስ ነው፡-

1. የጌታ ምለሳ በክርስቶስ የተሠግዎ፣ የማካተት እና የማየል ሙሉ አገልግሎት የክርስቶስ እንደ ማዕከላችን፣ እውነታችን፣ ሕይወታችን እና ሁሉ ነገራችን ምለሳ ነው—ቆላ. 1፡17፣ 18፤ መዝ. 80፡1፣ 15፣ 17-19፤ ዮሐ. 1፡14፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ራእ. 2፡4-5፣ 7፣ 17፤ 3፡7-8፣ 12-13፣ 17-22፤ 4፡5፤ 5፡6፤ ዮሐ. 6፡57፤ 14፡21፣ 23፤ 21፡15-17፤ ተዛ. ኤር. 32፡39።
2. የጌታ ምለሳ የክርስቶስ አካል አንድነት ምለሳ ነው—ዮሐ. 17፡11፣ 21-23፤ ኤፌ. 4፡3-4፤ ራእ. 1፡11።
3. የጌታ ምለሳ የሁሉም የክርስቶስ አካል ብልቶች አገልግሎት ምለሳ ነው—ኤፌ. 4፡15-16፤ ሮሜ 15፡16፤ 1 ጴጥ. 2፡5፣ 9፤ 1 ቆሮ. 14፡1፣ 4፣ 12፣ 26፣ 31፣ 39፤ ኤር. 31፡33-34 (በቁ. 33 ላይ ያለውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ)።

ሐ. ይህ ራእይ የሕይወታችን፣ የሥራችን እና የእንቅስቃሴያችን ሁሉ የሚቆጣጠር ራእይ እንዲሆን በውስጣችን ዕለት ዕለት መታደስ አለበት—1 ዮሐ. 1፡7፤ 1 ጴጥ. 2፡9፤ ኢሳ. 2፡5፤ መዝ. 119፡105፤ 36፡8-9።

መ. አንድ ሰው የጌታን ምለሳ ትቶ ሄደ ማለት የጌታ ምለሳ ምን እንደሆነ ፈጽሞ አይቶ አያውቅም ማለት ነው፤ የጌታ ምለሳን ራእይ ካላየን፣ በእርግጥም በጌታ ምለሳ ውስጥ አይደለንም—ሐዋ. 26፡13-19፤ ተዛ. ዘፍ. 13፡14-18።

ሠ. በጌታ ምለሳ ያለን እኛ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ የጠራ ራእይ ሊኖረን ይገባል፣ ከዚያም በዚያ ራእይ መገዛት፣ በቁጥጥሩ ሥር መሆን እና መመራት አለብን፣ ምክንያቱም በዚህ ያለነው የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ በምለሳው ለማከናወን ነውና።

ረ. በጌታ ምለሳ ያለው አመራር ግራ መጋባት እና ክፍፍል እንዳይኖር የሚገድበን፣ የሚመራን እና የሚቆጣጠረን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ በእግዚአብሔር-የተሰጠ ራእይ አመራር ነው—ምሳ. 29፡18።

ሰ. "ዘ ቪዥን ኦፍ ዘ ኤጅ" ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደውን ተጨማሪ ንባብ አንብቡ።

## III. የምለሳ መጻሕፍት የሆኑት የዕዝራ እና የነህምያ ማዕከላዊ እና ወሳኝ ነጥብ ተገቢው እና ብቁው አመራር ነው—ነህ. 8፡1-10፡-

ሀ. በጌታ ምለሳ ራእዩን በሚያመጡት ሰዎች በኩል በአንዱ አገልግሎት ውስጥ የአንዱ የሚቆጣጠረው ራእይ አመራር አለን—ኤፌ. 3፡3-5፣ 9፤ ቆላ. 1፡24-29፡-

1. ጳውሎስ እርሱ እና አብሮ-ሠራተኞቹ የ"ክርስቶስ ሎሌዎችና ...[የ]እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች" እንደነበሩ ተናግሯል (1 ቆሮ. 4፡1)፤ የእግዚአብሔርን ምሥጢራት ሰማያዊ ራእይ ለአማኞች የሚያድሉ መጋቢዎች ነበሩ፤ እነዚህ ምሥጢራት ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ምሥጢር እና ቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ ምሥጢር ናቸው (ቆላ. 2፡2፤ ኤፌ. 3፡4፤ 5፡32)፤ ይህ የማደል አገልግሎት፣ መጋቢነት የሐዋርያት አገልግሎት ነው (3፡2፣ 8-9)።
2. "በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል" (1 ቆሮ. 4፡2)፤ የእግዚአብሔርን እና የክርስቶስን ቃል እንደ የሕይወት አቅርቦት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአማኞች በማገልገል ለእግዚአብሔር ቤተሰብ ዘወትር መንፈሳዊ ምግብ የምንሰጥ ታማኝ ሎሌዎች ለመሆን (ማቴ. 24፡45-47) እንደ ጳውሎስ የታመንን እንሆን ዘንድ ከጌታ ምሕረትን የተቀበልን መሆን ያስፈልገናል (7፡25፤ 1 ጢሞ. 1፡12)፤ የጌታ ምዘና እና ሽልማት ስጦታውን በሙላት ከመጠቀም ታማኝነታችን ጋር እንጂ ከሥራችን ልክ እና ብዛት ጋር እንደማይገናኙ በመገንዘብ በሚቀጥለው ዘመን በጌታ ደስታ ውስጥ ለመሳተፍ በዚህ ዘመን በጌታ ሥራ ላይ የታመኑ መሆን እንፈልጋለን (25፡21-23፤ ተዛ. ራእ. 3፡8)።

ለ. እስራኤል የእግዚአብሔር ምስክር፣ በምድር ላይ ያለ የእግዚአብሔር መገለጥ እና ከአሕዛብ አገራት ፈጽሞ የተለየ ሕዝብ ሆና መልሳ መቀናበር የምትችለው እንደ ነህምያ እና ዕዝራ ባሉ ሰዎች አመራር ብቻ ነው፤ ይህ እግዚአብሔር ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን የሚፈልገው ነገር ምሳሌ ነው—ነህ. 13፡14፣ 29-31፤ 1 ጢሞ. 3፡15።

ሐ. ነህምያ ያለ ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መልሶ ማቀናበር እንደማይችል ያውቅ ነበር፡-

1. ሕዝቡን መልሶ ሲያቀናብር ነህምያ የእግዚአብሔርን ቃል እንደማያውቅ ተገነዘበ።
2. ዕዝራ በእግዚአብሔር ቃል እውቀቱ የታወቀ ነበረ፣ ነህምያ ደግሞ ከእርሱ እርዳታን ለመጠየቅ ፈቃደኛ ነበረ።

መ. በመለኮታዊው መርህ መሠረት፣ ተገቢው የአካሉ መወከል ያለው ሁልጊዜ ከሌሎች ጋር በተቀናኜ ሰዎች ነው—1 ቆሮ. 1፡1፤ ዘጸ. 4፡14-16፡-

1. ብቸኛ መሆን ግለኛ መሆን ነው፣ ከሌላ ሰው ጋር መላክ ግን በአካሉ መርህ መሠረት መላክ ነው—ሉቃ. 10፡1፤ ሐዋ. 13፡1-3፤ ሮሜ 12፡5፤ 1 ተሰ. 1፡1።
2. በግል መንቀሳቀስ የአካሉን መርህ መጣስ ነው።
3. በጌታ ምለሳ አካሉን የመገንባት እውነተኛ ሥራ አንገብጋቢ አስፈላጊነት አለ፤ ሆኖም ግን ይህ የግንባታ ሥራ መከናወን የሚችለው በተቀናጁ አብሮ-ሠራተኞች ብቻ ነው—ፊልጵ. 2፡19-22።

ሠ. "በመገጣጠም መንገድ ከእኔ ጋር እንደ ባልጀራ ባሮች አብረው የሚያገለግሉ ብዙ ወንድሞች እንዳዘጋጀ ጌታ አሳይቶኛል። ይህ ጌታ ለአካሉ ያለው ሉዓላዊ አቅርቦት እና አገልግሎቱን ለመፈጸም ያለው የዳበረ-የአሁኑ መንገድ እንደሆነ ይሰማኛል"—ዊትነስ ሊ፣ March 24, 1997 (*The Collected Works of Witness Lee, 1994-1997*, Vol. 5, "A Letter of Fellowship with Thanks," ከሚለው መጽሐፍ ከገጽ 525 የተወሰደ)።

***"ዘ ቪዥን ኦፍ ዘ ኤጅ"* ከሚለው የተወሰደ ተጨማሪ ጽሑፍ፡-**

**የተጠናቀቀውን የዘመኑን ራእይ አጥብቆ መከታተል**

ዛሬ እግዚአብሔርን ለማገልገል ራእያችን በዘፍጥረት ስለ አዳም ካለው የመጀመሪያው ራእይ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን መገለጥ እስከሆነችው እስከ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ ራእይ ድረስ መዝለቅ አለበት። የተጠናቀቀው ራእይ ይህ እና ይህ ብቻ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ይህ ራእይ ሙሉ በሙሉ አልተገለጠልንም ነበረ።

ታይፔይ በሚገኘው ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ሙዚየም ውስጥ በረዥም ጥቅልል ላይ የሚገኝ "የቺንግ-ሚንግ ፌስቲቫል ላይ ያለ የወንዝ ትእይንት" የሚል ስእል አለ። ስእሉ በተሳለበት ዘመን የነበረውን የቻይናዊያንን ባህል፣ ሕይወት እና መንገድ በዝርዝር ያብራራል። የዚያን የረዥም ጥቅልል [ስእል] የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ክፍሎች ብቻ ማየት በቂ አይደለም። አንድ ሰው በቻይና ያለውን መላው የሕይወት እይታ "ራእይ" ወይም ግልጽ ምስል ለማግኘት ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ጥግ ድረስ መሄድ አለበት። በተመሳሳይ መንገድ ለእግዚአብሔር ባለ አገልግሎታችን እኛም የራሳችን ስእል፣ የራሳችን "በቺንግ-ሚንግ የሚገኝ ወንዝ ትእይንት" አለን። በኤደን ገነት ከነበረው የአዳም የሕይወት ዛፍ ራእይ ጀምሮ የሕይወት ዛፍ እስካለባት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ድረስ ይዘልቃል። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በራእዩ ውስጥ ያለች የመጨረሻ ትእይንት ናት። ከዚያ በኋላ የሚታይ ተጨማሪ ነገር የለም።

...እግዚአብሔርን እያገለገልን ያለነው የቀደሙትን ትእይንቶች በሙሉ በሚያካትተው በመጨረሻው ትእይንት መሠረት ነው።

የዳበረው-የአሁኑ እና ከፍተኛው-የመጨረሻው-ምርጡ ራእይ ስላለን፣ እርሱን አጥብቀን መከታተል አለብን። በፍጹም ሰውን እየተከተልን አይደለም፤ ይልቁንም ራእይን እየተከተልን ነው። የሆነን ሰው እየተከተልን ነው ብሎ መናገር ትልቅ ስህተት ነው። የዚህ ዘመን የሆነውን ራእይ እየተከተልን ነው። ይህ የእግዚአብሔር የተጠናቀቀው ራእይ ነው።

የጌታ ምለሳ ወደ እኛ የመጣው በውድ ወንድማችን ኒ በኩል ነው። በዚህም ምክንያት እርሱ የጥቃቱ ዒላማ ሆኖ ነበር። በ1934 በሃንግቻው አገባ። አንዳንዶች ይህን አጋጣሚ ነውጥን ለማስነሳት ተጠቀሙበት። እርሱም በጣም አዘነ፣ ከዚህም የተነሣ አንድ ቀን ላጽናናው ወደ እርሱ ሄድኩ፣ እንዲህም አልኩት፣ "ወንድም ኒ በሁለታችን መካከል ተፈጥሮአዊ ግንኙነት እንደሌለ ታውቃለህ። አንተ እየወሰድክ ያለውን መንገድ የምወስደው ወይም አንተ እየሰበክ ያለውን ስብከት የምሰብከው ከአንተ ጋር ባለኝ ተፈጥሮአዊ ጓደኝነት አይደለም። ሁለታችን በጣም የተራራቅን ሰዎች ነን። እኔ የሰሜን ሰው ነኝ አንተ ደግሞ የደቡብ ሰው ነህ። ዛሬ ይህንኑ ተመሳሳይ መንገድ የምወስደው አንተን እንደ ሰው ስለምከተልህ አይደለም። እኔ የምከተለው አንተ የምትከተለውን መንገድ ነው። ወንድም ኒ ምን አልባት አንድ ቀን አንተ ይህን መንገድ ብትተወው እንኳ እኔ ይህን መንገድ እንደምከተል እንድታውቅ እፈልጋለሁ።" ይህን ያልኩበት ምክንያት ነውጡ አንዳንዶችን ስለነካና ከዚያ ወዲያ ይህን መንገድ ላለመከተል ስለወሰኑ ነበር። በሌላ አነጋገር ብዙ ሰዎች ሰውን እየተከተሉ ነበረ ማለት ነው። ያ የሚከተሉት ሰው የተለወጠ ሲመስል፣ መንገዱን ትተው ዘወር ይሉ ነበር። እኔ ግን ለወንድም ኒ እንዲህ አልኩት "ምን አልባት አንድ ቀን አንተ ይህን መንገድ ብትተወው እንኳ እኔ ይህን መንገድ እከተላለሁ። ይህንን

መንገድ የምከተለው በአንተ ምክንያት አይደለም፣ ይህን መንገድ ከአንተ የተነሣም አልተወውም። ይህ የጌታ መንገድ እንደሆነ አይቻለሁ። ራእዩን አይቻለሁ።”

ሃምሳ-ሁለት ዓመታት አልፈዋል። ዛሬ ስላደረኩት ነገር በፍጹም አልጸጸትም። ባለፉት ሃምሳ-ሁለት ዓመታት ተመሳሳይ ታሪክ  አሁንም አሁንም ሲደጋገም አይቻለሁ። አንዳንድ ሰዎች መጥተው ሄደዋል። አንድ ትእይንት ተቀይሯል፣ ሌላ ትእይንት ደግሞ አብሮት መጥቷል። በታይዋን ከነበረው ሥራችን ጀምሮ ላለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት ዋና ዋና የሚባሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አይተናል። እኔ ወደ መዳን የመራኋቸው እና በእኔ ስልጠና ውስጥ ያለፉ ወንድሞች እንኳ ሳይቀር የጌታ ምለሳን ትተው ሄደዋል። ራእዩ በፍጹም አልተለወጠም፣ ሰዎቹ ግን በእርግጥም ተለውጠዋል፣ ራእዩን ይከተሉ የነበሩ ሰዎችም ጭምር ተለውጠዋል። ከልቤ ለሁላችሁም ግልጽ ቃል እናገራለሁ። በጌታ ምሕረት ይህን ራእይ ለእናንተ ለማቅረብ መቆም ችያለሁ። እኔን እንደ ሰው እንደማትከተሉ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ያሳየኋችሁን ራእይ በጌታ ምሕረት እንደምትከተሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

አንድን ሃቅ ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። ራእዩን ለእኔ መግለጡ የጌታ ምሕረት ነው። ወንድም ኒ እና በዘመናት ሁሉ የነበሩ የጌታ አገልጋዮች በሙሉ ትተውልን ያለፉትን እና እኔ ለእናንተ ያስተላለፍኩትን ይህን ራእይ እንድትከተሉ እንጂ እኔን እንዳትከተሉ እመክራችኋለሁ። ይህ በእርግጥም ከመጀመሪያው የአዳም ትእይንት እስከ የመጨረሻው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትእይንት የሚዘልቅ ራእይ ነው (ገጽ. 48-50)።

© 2022 Living Stream Ministry